ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ሰኔ 1998 ዓ.ም.

# የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች

ቁጥር 5

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው።

- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል::

- በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን እያካሄደ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት ለመወያያ የቀረበው ርዕስ *የምግብ ዋስትናን በኢትዮጵያ ማረጋገጥ ይቻላል?* የሚል ነው።

- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን።

## ድሃነት እና የሴተኛ አዳሪነት ማህበራዊ ገጽታ በአዲስ አበባ

### ሀ. መግቢያ

በኢትዮጵያ በሴተኛ አዳሪነት ላይ ያተኮሩ ጥናታዊ ጹሁፎች ከተቀረው የአፍሪካ ክፍል እና በተለይም ከምዕራቡ ዓለም በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ካተኮሩ ጥናታዊ ጹሁፎች ጋር የሚጋሩዋቸው አመለካከቶች አሉ:: እነዚህን አመለካከቶች በሶስት ክፍሎ ማየት ይቻላል::

**ሴተኛ አዳሪዎችን ከሰራቸው ለይቶ አለማየት**

በሴተኛ አዳሪነት ሰራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ባህሪ እና ማኅበራዊ ማንነት በሚሰሩት ሰራ ይገለጻል የሚል የቆየ አመለካከት በምዕራቡ ዓለም አለ:: በኢትዮጵያም ሴተኛ አዳሪዎችን ከሴተኛ አዳሪነት ሰራ ለየቶ አለማየት ሁኔታ አለ:: በመሆኑም በቅርቡ ከኤች አይቪ/ኤይድስ (HIV/AIDS) ጋር ተያይዞ ሴተኛ አዳሪዎችን በሕብረተሰብ ላይ ችግር ፈጣሪ ወይም የሕብረተሰብ ጠንቅ አድርጎ የመመልከት ሁኔታ ጨምሯል::

**ሴተኛ አዳሪዎችን በጥቅሉ መመልከት**

በተለይ በምዕራቡ ዓለም ሴተኛ አዳሪዎችን በተመለከተ ሁለት ዋነኛ ሊባሉ የሚችሉ ተጻራሪ አመለካከቶች አሉ:: 1ኛ:- በሴተኛ አዳሪነት ሰራ ላይ የተሰማሩትን ሴቶች በሕብረተሰብ ላይ ጉዳት አምጪዎች አድርጎ መመልከት፣ 2ኛ:- ሴተኛ አዳሪዎችን ለወንዶች አድሎ በሚያደርግ ሥርዓት ተጠቂ የሆኑ ሴቶች አድርጎ መመልከት:: እነዚህ ሀሳቦች ተጻራሪ ቢሆኑም ሁለቱም ሴተኛ አዳሪዎችን በጥቅሉ ነው የሚመለከቱት:: ይህ አመለካከት በኢትዮጵያም ውስጥ በጉልህ ይንፀባረቃል::

**ሴተኛ አዳሪዎችን በራሳቸው ጉዳይ ባለቤት አድርጎ አለመውሰድ**

በአውሮፓ እ.አ.አ በ1960ዎቹ እና በ70ዎቹ ከነበረው የሴቶች እንቅስቃሴ በፊት በሴተኛ አዳሪነት ላይ ይደረጉ የነበሩ ጥናቶች ለሴተኛ አዳሪዎች ሀሳብ ትኩረት አይሰጡም ነበር:: በኢትዮጵያም እስከ አሁን ድረሰ ሴተኛ አዳሪዎች ስለራሳቸው ሕይወት በሰፊው እንዲናገሩ ዕድል የመስጠት ሁኔታ አልተለመደም::

በቅርቡ በማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) የታተመው የወ/ት ቤተልሔም ተኮላ ጥናት አዲስ አበባ በሚገኙ ሴተኛ አዳሪዎች ማኅበራዊ ሕይወት ላይ በማተኮር የነዚህን አመለካከቶች ጉድለት ለማመላከት ሞክሯል:: ጥናቱ ዐሀዛዊና ዐሀዛዊ ያልሆኑ መረጃዎችን ተጠቅሟል:: ዐሀዛዊ ያልሆኑ መረጃዎች የተገኙት በሴተኛ አዳሪነት ሰራ ላይ የተሰማሩትን ሴቶች በግልና በቡድን በማናገር እንዲሁም ያላቸውን ማኅበራዊ ሕይወት በመመልከት ሲሆን ዐሀዛዊ መረጃ የተሰበሰበው ለ100 ሴተኛ አዳሪዎች በተዘጋጀ መጠይቅ ነው::

### ለ. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

በሴተኛ አዳሪነት ስራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ከተለያየ የህብረተሰብ ክፍል ጋር ያላቸው ማኅበራዊ ግኑኙነት ላይ በማተኮር ጥናቱ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙትን ሴተኛ አዳሪዎች እርስ በእርስ የሚያመሳስሏቸውና የሚለያይዋቸውን መስፈርቶች ለይቶ ለማስቀመጥ ሞክሯል:: ከዚህ በፊት የነበሩ ጥናቶች ሴተኛ አዳሪዎችን ለመመደብ የተጠቀሙበት መስፋርት በሚሰሩት የሴተኛ አዳሪነት ስራ ዓይነት ላይ ብቻ ያተኮረ ነበር:: ይህ ጥናት ግን በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙትን ሴተኛ አዳሪዎች ለመመደብ ከሚሰሩት የሴተኛ አዳሪነት ስራ ዓይነት በተጨማሪ አራት መስፈርቶችን አካቷል:: እነዚህም:-

- የሴተኛ አዳሪዎች የግልና የቤተሰብ የኋላ ታሪክ፣
- ሴተኛ አዳሪዎቹን ወደዚህ ስራ እንዲገቡ ያደረጉዋቸው ምክንያቶች፣
- የሴተኛ አዳሪዎቹ የቤት እና

የአኗኗር ሁኔታ፣

- የሴተኛ አዳሪዎች በመረዳዳት ላይ የተመሰ ረተ ማኅበራዊ ግንኙነት ናቸው::

## የሴተኛ አዳሪነት ስራ አይነቶች በአዲስ አበባ

በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ሰባት ዓይነት የሴተኛ አዳሪነት ስራ ዓይነቶች አሉ:: እነዚህም የሴተኛ አዳሪነት ስራ ዓይነቶች በሁለት መስፈርቶች ላይ ተ መስርተው የተሰየሙ ናቸው::

### ሀ/ ሴተኛ አዳሪዎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ቦታ

በዚህ መስፈርት ላይ ተመስርተው የተሰየሙ የሴተ ኛ አዳሪነት ስራ ዓይነቶች አራት ናቸው:: እነዚህም: - አስፋልት ላይ የሚሰሩ፣ መጠጥ ቤት የሚሰሩ፣ ቡና ቤት የሚሰሩ፣ ሆቴል/ክለብ የሚሰሩ::

### ለ/ ሴተኛ አዳሪዎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ሁኔታ

በዚህ መስፈርት ላይ ተመስርተው የተሰየሙ የሴተ ኛ አዳሪነት ስራ ዓይነቶች ደግሞ ሶስት ናቸው:: እነዚህም:- በአልጋ የሚሰሩ፣ እኩል አካፋይ የሆኑ፣ የተወሰነ አካፋይ የሆኑ::

### አጭር መግለጫ

1. **አስፋልት ላይ የሚሰሩ:-** እነዚህ ሴቶች አስፓልት ዳር በመቆም በአብዛኛው ባለመኪና ወይም አልፎ አልፎ እግረኛ ወንዶችን ይጠባበቃሉ:: ብዙዎቹ አዲሰ አበባ ተወልደው ያደጉ ወይም ከሌላ ከተማ የመጡ ሴቶች ናችው:: በዚህ ዓይነት ሰራ ላይ የተሰማሩ ጥናቱ ውስጥ የተካተቱት ሴቶች አማካኝ እድሜ 22 ዓመት ነው:: ይህ ዓይነት የሴተኛ አዳሪነት ስራ በተለይ ከ1983 ወዲህ እየጨመረ ነው የመጣው::
2. **መጠጥ ቤት የሚሰሩ:-** እዚህ ሁለት ዓይነት ሴተኛ አዳሪዎች አሉ:: እነዚህም በቋሚነት የሚሰሩና ተመላላሽ የሆኑ ናቸው:: በቋሚነት የሚሰሩት ከመጠጥ ቤቱ የማደሪያና የምግብ አገልግሎት ያገኛሉ:: በአብዛኛው መጠጥ ቤቱን የቤት ስራ በመስራት ያግዛሉ፣ ከዚህም በተ ጨማሪ ከወንድ ጋር ከመጠጥ ቤቱ ውጪ “ለመተኛት” ሲወጡ “መውጫ ይቆርጣሉ” (ከ5-15 ብር ለመጠጥ ቤቱ ይከፍላሉ):: ተመላላሽ ሆነው የሚሰሩት ከምሽቱ 12 በኋላ ሰራ ይገባሉ:: መጠጥ ቤቱን በማስተናገድ ይረዳሉ፣ በተጨማሪም እንደ ቋሚዎቹ ከወንድ ጋር “ለመተኛት” ከመጠጥ ቤቱ ውጭ ሲወጡ “መውጫ ይቆርጣሉ”::
3. **ቡና ቤት የሚሰሩ:-** እዚህም ሁለት አይነት ሴተ ኛ አዳሪዎች አሉ:- አስተናጋጆች/የቤት ልጆች እና አሻሻጮች:: አስተናጋጆች/የቤት ልጆች የሚባሉት በቁጥራችው አነሰተኛ ሆነው የቡና ቤ ቱ የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪዎች ናችው:: ከነዚህ ውሰጥም የማታና የጠዋት ገቢዎች አሉ:: አሻሻጮች አመሻሽ ላይ መጥተው ቤቱ እስከሚዘጋ ይሰራሉ:: እነዚህ ሴቶች የቤቱ ተ ቀጣሪዎች አይደሉም፣ ለቤቱ ዋነኛ ሰራችው መጠጥ ማሻሻጥ ነው:: ሁለቱም ዓይነት ሴተኛ አዳሪዎች ከቡና ቤቱ ውጪ ከወንድ ጋር “ለመተኛት” ሲወጡ “መውጫ ይቆርጣሉ” (ከ5-15 ብር ለቡና ቤቱ ይከፍላሉ)::
4. **ሆቴል/ክለብ የሚሰሩ:-** በአብዛኛው ሆቴል/ክለብ እየገቡ የሚሰሩ ሴቶች አስፋልት ላይ የሚሰሩ ሴቶች ናቸው:: ነገር ግን ሌሎች ሴቶችም ሆቴ ል/ክለብ በመግባት ይሰራሉ:: በአንጻራዊነት የእነዚህ ሴቶች የኢኮኖሚ አቅም ከፍ ያለ ነው::
5. **በአልጋ የሚሰሩ:-** እነዚህ ሴተኛ አዳሪዎች በአነስተኛ የቀበሌ/ የቀበሌ ቤት ከሚያከራዩ ግለሰቦቸ ተከራይተው (በብዛት አንድ ክፍል) ውሰጥ በራሳቸው አልጋ ላይ የሚሰሩ ናቸው:: በብዛት ቤቱ በር ላይ በመቆም ወንዶችን ይጠባበቃሉ::
6. **እኩል አከፋይ የሆኑ:-** እነዚህ ሴተኛ አዳሪዎች በአነሰተኛ ቤት (በብዛት አንድ ክፍል) ውሰጥ በአሰሪዎቻችው አልጋ ላይ የሚሰሩ ናችው:: ቤ ቱና አልጋው የአሰሪዎቻችው ሰለሆነ (ከቀበሌ/ የቀበሌ ቤት ከሚያከራዩ ግለሰቦቸ ተከራይተው) ለነዚህ ሰዎች (በብዛት ሴቶች ናችው) በዚህ ሰራ ከሚያገኙት ገቢ እኩሌታውን ያካፍላሉ:: በአልጋ እንደሚሰሩት ሴቶቸ በብዛት ቤቱ በር ላይ በመቆም ወንዶችን ይጠባበቃሉ::
7. **የተወሰነ አከፋይ የሆኑ:-** እነዚህ ሴቶች ከእኩል አካፋይ ሴቶች ጋር የሰራ ሁኔታቸው ይመሳሰላል የሚለዩት በዚህ ሰራ ከሚያገኙት ገቢ የተወሰነውን (እንደስምምነታቸው) ለአሰሪዎ ቻችው በመሰጠታቸው ነው::

## የሴተኛ አዳሪዎች የግልና የቤተሰብ የኋላ ታሪክ

**ዕድሜ:-** በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ሴተኛ አዳሪ ዎች በአብዛኛው በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው:: ብዙዎቹ ወደዚህ ስራ ሲገቡ ዕ ድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ነበር:: የጥናቱ መ ረጃ የተሰበሰበባቸው ሴተኛ አዳሪዎች አማካኝ ዕድሜ 23 ዓመት ነው::

**የጋብቻ ሁኔታ:-** የጥናቱ ዐሀዛዊ መረጃ እንደሚያመለክተው አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ሴተኛ አዳሪዎች (65%) አንድም ጊዜ ያላገቡ ናቸው:: አግብተው ከነበሩት ውስጥ 94.2% ወደ ሴተኛ አዳሪነት ስራ ከመግባታቸው በፊት እንደተፋቱ ሲገልፁ 5.7% ባላቸው እንደሞተባችው አመልክተ ዋል:: ወደ ሴተኛ አዳሪነት ስራ ከመግባታችን በፊት አግብተን ነበር ያሉት ሴቶች በሙሉ ትዳር የያዙት 20 ዓመት ሳይሞላቸው ነበር::

**የትውልድ ቦታ:-** ከጥናቱ የተገኘው ዐሀዛዊና ዐሀዛዊ ያልሆነ መረጃ እንደሚያመለክተው በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ሴተኛ አዳሪዎች አዲስ አበባ ተወልደው ያደጉ ወጣት ሴቶች ናቸው:: መ ረጃ ከተሰበሰበባቸው ሴቶች መከከል 52% አዲስ አበባ ተወልደው ያደጉ ሲሆን 48% ከተለያየ የሀገሪ ቱ ክፍል ፈልሰው የመጡ እንደሆነ አመልክተዋል:: ከአዲስ አበባ ውጪ መጣን ካሉት ውስጥ 24% ብቻ ናቸው ከገጠር አካባቢ የመጡ:: ይህም ማለት አብዛኛዎቹ ሴተኛ አዳሪዎች (76%) ከከተማ አከባቢ የመጡ ናቸው::

**የአስተዳደግ ሁኔታ፡-** መረጃ ከተሰበሰበባቸው ሴቶች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት (59%) በሁለት ወላጆች አላደጉም:: ከነዚህም ውስጥ 31% በአንድ ወላጅ ብቻ፣ 13% በሌላ ዘመድ፣ 9% በአያቶቻቸው፣ 5% በአንድ ወላጅና በእንጀራ ወላጅ፣ 1% በእንጀራ ወላጅ ብቻ እንዳደጉ ገልፀዋል:: 51% ደሀ ከሚባል ቤተሰብ የመጡ ሲሆን፣ 43% እራሱን ከሚችል ቤተ ሰብ 6% ደግሞ ሀብታም ከሚባል ቤተሰብ እንደመጡ አመልክተዋል::

**የትምህርት ደረጃ፡-** መረጀ ከተሰበሰበባቸው ሴተኛ አዳሪዎች መካከል 24% ት/ቤት አልገቡም:: 46% የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (እስከ 6ኛ ክፍል ወይም በታች)፣ 18% የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተ ከታትለው እንደነበር ሲያመለክቱ 2% አሁንም ይህንን ስራ እየሰሩ እንደሚማሩ ጠቁመዋል:: በአጠቃላይ ከሴተኛ አዳሪዎቹ መካከል 63% ትምህርታቸውን ያቋረጡ ናቸው::

**ሴተኛ አዳሪዎቹን ወደዚህ ስራ እንዲገቡ ያደረጋቸው ምክንያት**

በአዲስ አበባ የሚገኙ ሴተኛ አዳሪዎች ወደዚህ ስራ ለመግባታቸው ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በሁለት ከፍሎ ማየት ያስፈልጋል::

1ኛ:- በተዘዋዋሪ ወደዚህ ስራ ለመግባት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች፤ እነዚህም:-

- የቤተሰብ የገንዘብ ችግር (63%)
- በዘመድ ወይም በጓደኛ አነሳሽነት ወደዚህ ስራ መግባት (21%)
- በቤተሰብ የሚደርስ ጥቃት ወይም ከቤተ ሰብ ጋር አለመስማማት (10%)
- በከተማ ኑሮ መሳብ (3%)

2ኛ:- በቀጥታ ወደዚህ ስራ ለመግባት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች፤ እነዚህም:-

- ሌላ ስራ አለማግኘት (53%)
- የጓደኛን ምሳሌ መከተል (20%)
- በስራ አስቀጣሪ ደላላዎች እና የሴተኛ አዳሪ ቀጣሪ በሆኑ ሰዎች በመታለል (20%)
- ሳያስቡት አንድ ነገር ሌላን አስከትለሎ ገባን የሚሉ (7%)

**የሴተኛ አዳሪዎች የቤት እና የአኗኗር ሁኔታ**

በዐሀዝ ላይ የተመሰረተው የጥናቱ መረጃ እንደሚያመለክተው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሴተኛ አዳሪዎች (54%) የሚኖሩት እዚያው የሚሰሩበት ቦታ ነው:: ከነዚህም ሴቶች አብዛኛዎቹ ቤቱን ከቀበሌ ወይም የቀበሌን ቤት ከሚያከራዩ ግለሰቦች እነሱ ወይም አሰሪዎቻቸው እንደተከራዩት አመልክተዋል::

**የሴተኛ አዳሪዎች በመረዳዳት ላይ የተመሰረተ ማህበራዊ ግንኙነት**

በሴተኛ አዳሪነት ስራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ማህበራዊ ህይወት ደካማ ነው ከሚለው የተለምዶ አስተሳሰብ በተፃራሪ በሴተኛ አዳሪነት ስራ ላይ የተ ሰማሩ ሴቶች ጠንካራ የሆነ ማህበራዊ ግንኙነት እንዳላቸው ጥናቱ ያመላክታል:: በአዲስ አበባ ውስጥ አማካኝ የሚሆኑ ሴተኛ አዳሪዎች ወደ ሴተ ኛ አዳሪነት ስራ ከመግባታቸው በፊት የነበራቸውን ማህበራዊ ግንኙነት ለማቆየት የሚታገሉ ወይም ስራው ውስጥ ከገቡ በኋላ አዲስ ማህበራዊ ትስስር ለማዳበርና ለማቆየት የሚፋጨረጨሩ ሴቶች ናቸው:: ስለዚህ በተለይ አውሮፖና ሰሜን አሜሪካ ጉልቶ የሚታየው አስተሳሰብ ማለትም ሴተኛ አዳሪ ለብቻዋ ሰርታ ለብቻዋ የምትኖር ሴት ናት የሚለው አዲስ አበባ ውስጥ እውነት የመሆኑ ሁኔታ በጣም አነስተኛ ነው:: ጥናቱ ከተሰበሰበባቸው ሴተኛ አዳሪ ዎቸ መካከል 74% ከቤተሰብ ጋር ግኑኝነት አለን ሲሉ 22% የለንም፣ 2% ከተወሰኑ የቤተሰብ አባል ጋር ግኑኝነት አለን፣ 2% ቤተሰብ የለንም ብለዋል:: 38% የሚሆኑት ሴተኛ አዳሪዎች በሚያገኙት ገንዘብ ሙሉ በሙሉ የሚያስተዳድሩት የቤተሰብ አባል እንዳለ ሲናገሩ 46% የሚሆኑት ደግሞ በከፊል ድጋፍ የሚያደርጉላቸው ሰዎች እንዳሉ አመልክተ ዋል::

## ሐ. ለፖሊሲ ጠቀሜታ ያላቸው ነጥቦች

1. ከጥቂት ዓመታት ወዲህ አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ሴተኛ አዳሪዎች በአብዛኛው እዚሁ ከተ ማ ወስጥ ተወልደው ያደጉ ሴቶች የመሆናቸው ሁኔታ እየጨመረ ነው የመጣው:: ድሮ የአዲስ አበባ ሴተኛ አዳሪዎች በአብዛኛው ትምህርት ቤ ት ያልገቡ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ፈልሰው የመጡ ሴቶች ነበሩ:: አሁን ግን የአዲስ አበባ ሴተኛ አዳሪዎች በአብዛኛው ትምህርታቸውን ያቋረጡ ከተማው ውስጥ ተወልደው ያደጉ ሴቶች ናቸው:: ይህም ማለት ወደ ሴተኛ አዳሪነት ስራ ሊያስገቡ የሚችሉ ምክንያቶች በዋናነት ከተማ ውስጥ ካሉ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ጋር የተያያዙ ናቸው::

2. ሴተኛ አዳሪዎችን በጥቅሉ መመልከት ትክክል አይደለም:: እንደማንኛውም ሰው በሴተኛ አዳሪነት ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሴቶች እርስ በእርስ የሚያመሳስሏቸው ወይም የሚያለያይዋቸው ባህሪያት አሏቸው:: በመሆኑም የሚያመሳስላቸው ጉዳይ ላይ ማለትም ስራቸው ላይ ብቻ ማተኮር ተገቢ አይደለም:: ስራቸው ላይ እንኳ ብናተኩር ሴተኛ አዳሪዎች በሚሰሩት የሴተኛ አዳሪነት ስራ ዓይነት ይለያያሉ:: ከኤች አይቪ/ኤይድስ (HIV/ AIDS) ጋር በተያያዘ አንዱ የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው በሴተኛ አዳሪነት ስራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ለኤች አይቪ (HIV) የመጋለጣቸው ሁኔታ በሚሰሩት የሴተኛ አዳሪነት ስራ ዓይነት ይለያያል:: ለምሳሌ አካፋይ ሆነው የሚሰሩ ሴቶች በራሳቸው አልጋ ከሚሰሩ ሴቶች የበለጠ ለቫይረሱ የተጋለጡ ናቸው:: በራሳቸው አልጋ የሚሰሩ ሴቶች አንጻራዊ የስራ ነፃነት ሲኖራቸው አካፋይ ሆነው

የሚሰሩ ሴቶች ነፃነት ግን በአሰሪዎቻቸው የተገደበ ነው፡፡ ለምሳሌ ኮንዶም አልጠቀምም የሚል ወንድ ቢያጋጥማቸው አካፋይ ሴቶች በአሰሪዎቻቸው ተገደው ሊያስተናግዱ ሲችሉ በአልጋ የሚሰሩት ግን እንቢ የማለት ነፃነት አላቸው፡፡

3. ከኤች አይቪ/ኤይድስ (HIV/AIDS) ጋር በተያያዘ ሌላው የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው በሴተኛ አዳሪነት ስራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ለቫይረሱ በዋነኝነት የሚጋለጡት ብር ከፍለው ከነሱ ጋር "ለመተኛት" ከሚመጡ ወንዶች ጋር ባላቸው ግኑኝነት ሳይሆን እነዚህ ሴቶች "ያስከብረኛል" ብለው ከሚይዟቸው "ባሎች" ወይም "ፍሬንዶች" ጋር ባላቸው ልቅ የሆነ የግብረ ስጋ ግኑኝነት ነው፡፡

4. ሴተኛ አዳሪነትን በዚህ ስራ ከሚተዳደሩ ሰዎች ለይቶ ማየት ያስፋልጋል፡፡ ብዙ ጊዜ ሴተኛ አዳሪነትን ለመቀነስ፣ ስርጭቱን ባለበት ለማሰቀም ወይም በአጠቃላይ ለማጥፋት እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ እንመለከታለን፡፡ ነገር ግን ብዙውን ጊዜ እነዚህ እንቅስቃሴዎች ሴተኛ አዳሪነትን ይህን ስራ ከሚሰሩ ሴቶች ለይተው ስለማይመለከቱ ውጤታቸው ሴተኛ አዳሪዎችን ከተወሰነ አካባቢ /ቦታ/ በኃይል ከማስለቀቅ ወይም በአደባባይ እንዳይንቀሳቀሱ ከማድረግ የዘለለ አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር እነዚህ እንቅስቃሴዎች ወደ ሴተኛ አዳሪነት ስራ ለመግባት ምክንያት ለሆኑ ችግሮች መፍትሔ ከማፈላለግ ይልቅ ሴተኛ አዳሪዎች በኃይል ከዚህ ስራ እንዲወጡ በማድረግ ላይ በማተኮራቸው ውጤታማ አይደሉም፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ጥናቱ እንደሚያመለክተው አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ ሴተኛ አዳሪዎች ከዚህ ስራ በሚያገኙት ገንዘብ የሚያስተዳድሯቸው ወይም ደግሞ የሚረዷቸው ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ በመሆኑም ሴተኛ አዳሪነትን ለመቀነስ ወይም ለማጥፋት በሚደረግ እንቅስቃሴ ሁሉ እነዚህን ሰዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፍልጋል፡፡

5. በአዲስ አበባ የሴተኛ አዳሪነት ስራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቤትንና ከቤት ውጪ ያለን ቦታ ከመቆጣጠር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በሴተኛ አዳሪነትና በቤት መከከል ያለው ግኑኝነት ብዙውን ጊዜ ትኩረት አይሰጠውም፡፡ ነገር ግን በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ የሴተኛ አዳሪነት ስራ ዓይነቶች ከቤት ጋር ያላቸው ቁርኝት ከፍተኛ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ሴቶች በአንድ ዓይነት የሴተኛ አዳሪነት ስራ ለመግባት ሲወስኑ ከስራው ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የቤት እና የአኗኗር ሁኔታ ለመቀበል ይገደዳሉ፡፡ እንዲያውም አሁን ባለው ሁኔታ ሴቶች የሚገቡበት የሴተኛ አዳሪነት ስራ ዓይነት የቤት እና የአኗኗር ሁኔታቸውን ይወስን ወይም የቤት እና የአኗኗር ሁኔታቸው የሚገቡበትን የሴተኛ አዳሪነት ስራ ዓይነት ይወስን እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም፡፡ ከቤት ውጪ ያለን ቦታ መቆጣጠር አስፋልት ላይ ከሚሰሩ ሴቶች ጋር ይያያዛል፡፡ አንድን አካባቢ በጉልበት የሚቆጣጠሩ ሰዎች (ወንዶች እና ሴተኛ አዳሪዎች ጭምር) በዚያ አካባቢ የሚሰሩ ሴተኛ አዳሪዎችን የስራ እንቅስቃሴ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይቆጣጠራሉ፡፡

6. ወደ ሴተኛ አዳሪነት ስራ ለመግባት በቀጥታ ምክንያት ናቸው ተብለው በጥናቱ ውስጥ በተካተቱት ሴቶች ከተጠቀሱት ጉዳዮች መካከል በስራ አስቀጣሪ ደላላዎች መታለል በሁለተኛ ደረጃ ይገኛል፡፡ በብዛት ከክፍለ ሀገር የሚመጡ ሴቶችን "የተሻለ ስራ አስቀጥራችኋለሁ" በማለት ወደ ሴተኛ አዳሪነት ስራ የሚያስገቡ ብዙ ደላላዎች እንዳሉ ጥናቱ ያመለክታል፡፡ ስለዚህ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ስራ አስቀጣሪ ደላላዎችን የስራ እንቅስቃሴ መቆጣጠር ተገቢ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዐሀዛዊ ያልሆነው የጥናቱ መረጃ እንደሚያመለክተው በቤት ሰራተኛ ቀጣሪዎች የሚደርስ በደል ለብዙ ሴቶች ወደ ሴተኛ አዳሪነት ስራ መግባት ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም በከተማው ውስጥ የቤት ሰራተኞችን መብትና ግዴታ ሊቆጣጠር የሚችል አካል ቢኖር በዚህ ምክንያት ወደ ሴተኛ አዳሪነት ስራ የሚገቡትን ሴቶች ቁጥር መቀነስ ይቻላል፡፡

7. በመጨረሻ በአጠቃላይ የሴቶችን በተለይም ደግሞ በተለያየ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጉዳዮች ተጨቁነው የሚገኙ ሴቶችን አቅም ማጎልበት (ለምሳሌ ለቀድሞ ሴተኛ አዳሪዎች ገቢ የሚያስገኝ ስራ በመፍጠር) ሴተኛ አዳሪነትን ለመቀነስ፣ ስርጭቱን ባለበት ለማሰቀም ወይም በአጠቃላይ ለማጥፋት በሚደረግ ጥረት ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡

**ምንጭ:-** Bethlehem Tekola. *Poverty and the Social Context of Sex Work in Addis Ababa: An Anthropological Perspective*. Addis Ababa: FSS, 2006.

**Address: Forum for Social Studies ♦ P. O. Box 25864 code 1000 ♦ Addis Ababa, Ethiopia**
**Telephone: 251-111-572 -990/91 ♦ Fax: 251-111-572-979**
**E-mail: fss@ethionet.et ♦ Home page: www.fssethiopia.org.et**